የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፮ ቀን ፪ሺ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 41.
ADDIS ABABA 3rd June, 2008

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፭/፪ሺ ዓ.ም

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በግብር ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቼክ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ...... ገጽ ፬ሺ፩፻፲፬

<u>**CONTENTS**</u>

**Proclamation No. 585/2008**

Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Czech Republic for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation Page 4114

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፭/፪ሺ

## <u>በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በግብር ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቼክ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቼክ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በግብር ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት እ.ኤ.አ. ጁላይ ፳፭ ቀን ፪ሺ፯ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክ ራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገ - መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ «በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚ መለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በግብር ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቼክ ሪፐ ብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፭/፪ሺ» ተብሎ ሊጠ ቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 585/2008.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE CZECH REPUBLIC FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVENTION OF FISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME

**WHEREAS,** the Agreement for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income (the Convention) was signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Czech Republic in Addis Ababa on the 25th day of July 2007;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified thisAgreement at its session held on the 15th day of May, 2008;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

### 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Czech Republic for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No. 585 /2008".

## ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቼክ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፳፭ ቀን ፪ሺ፯ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በግብር ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችለው ስምም ነት ፀድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፳፮ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Czech Republic for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income signed in Addis Ababa on the 25th day of July 2007 is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to implement the agreement in collaboration with the concerned Government organs.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of June, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**